# አፍራሽ ድርጊታቸው ወያኔን ለመጥቀም ካልሆነ ማንን?
# ፍርዱንና ቆራጥ አቋም መያዙን ለሕዝብ

የቅንጅት መሪዎች ከእስር ከተፈቱ በኋላ ትግሉን ከደከመበት አንስተው ቀድሞ ወደ ነበረበት ሁኔታ ይመልሱታል የሚል ትልቅ ተስፋ ነበረን። በውጭ አገር ተከስቶ የነበረው ችግርም አገር ቤት ገብቶ መሪዎቻችንን እንዳይከፋፍል የሚልም ስጋት ይዞን ስንጨነቅ ከረምን። ሆኖም ግን ሁኔታዎችን በትክክለኛው ደረጃና መንገድ ባለማወቃችን ነበር የያኔው ስጋታችን። የችግሩ መንስዔ ከየት እንደጀመረ በሚገባ ያወቅነው በመስከረም መጀመሪያ ላይ ወደ አሜሪካ የመጣው አምስት የቅንጅት አመራሮች ቡድን ለብቻው የግል ዓላማውን ማራመድ ሲጀምር ነው። ቡድኑ የሰራውን ሁሉ በማስረጃ ያረጋገጥነውና ዛሬም በአይናችን እያየን ያለው አፍራሽ እንቅስቃሴ በእርግጥ እንደወያኔ ቅንጅትን ሊያጠፋ ቆርጦ የተነሳ ቡድን ወይም ክፍል መሆኑን እያሳየን ነው።

የእነ ወይዘሮ ብርቱካን ቡድን በሰሜን አሜሪካ በየከተማው ሲዞሩ ከሌላው ወገን የተሰራ ማሰናከያ ወይም ስብሰባዎቻቸውን ለማደናቀፍ የተደረገ አንዳችም ሙከራ አልነበረም። መሪዎቻችን ተከፋፍለው ሳይሆን ከፓርቲው ፕሬዚዳንት ጋር ሆነው እንዲመጡ ብዙ የድጋፍ ድርጅቶች መግለጫ ማውጣታቸው ይታወሳል። ሆኖም ግን ያንን ችላ ብለው በራሳቸው ፕሮግራም በየከተማው ዞረውና ገንዘብ አሰባስበው ከፊሉም ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ ሌላውም እዚሁ ቀርቷል።

የቅንጅት ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ሕክምናቸውን አጠናቀው ደጋፊዎቻቸውን ለማመስገንና ለማወያየት በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ግን ሌላው ቡድን እግር በእግር እየተከታተለ በሚሄዱበት ከተማ ሁሉ ስብሰባ እየጠራ ሕዝቡን ግራ ማጋባቱና አፍራሽ ቅስቀሳ ማካሄዱ ግን ቅንጅትን ለማዳከምና ለማፈራረስ የወያኔን ስራ እየሰራ ከመሆኑ በቀር ሌላ ሊባል የሚችለው ነገር የለም።

ልብ ብላችሁ አስተውላችሁ ከሆነ በሚኒያፖሊስ፣ በሲያትል፣ በአትላንታ እና አሁን ደግሞ በኦክላንድ ተመሳሳይ ስራ እየተደረገ ነው። ይባስ ተብሎ ስብሰባ ሲካሄድ ብዙ ወጪዎች እንዳሉ እየታወቀ ያንን ለመሸፈኛ በድጋፍ ድርጅቶች የሚደረገውን አስተዋጽኦ ለመቀናቀን የእነ ዶክተር ብርሃኑ ቡድን ስብሰባ መግቢያ በነጻ እና አዝናኝ አርቲስቶች በነጻ አለ በማለት ማስታወቂያ አውጥተው ሕዝብን ግራ እያጋቡ ነው። ለመሆኑ ወጪው ከየት መጥቶ ይሸፈናል? ይህ በትክክል የኢንጂነር ኃይሉን የጉብኝት ፕሮግራም ለማጨናገፍ የታቀደ ሴራ ነው። በውጭ አገር ያለህ ወገን ሁሉ ይህንን አፍራሽ ድርጊታቸውን ተመልክተህና ዓላማቸው ምን እንደሆነ ተገንዝበህ የራስህን እርምጃ እንድትወስድና ፍርድ እንድትሰጥ እንጠይቃለን።

የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ በአደገኛና በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ እያለ የተጀመረውን የሕዝብ ትግል ለማኮላሸትና ለማዳከም በተመሳሳይ ከተማና ቀናት ስብሰባ ከማድረግም አልፎ አርቲስቶች እንደማንኛውም ዜጋ ሁሉ የድጋፍ ድርሻቸውን በገንቢ ሁኔታ ማበርከት ሲገባቸው ለአፍራሽ ድርጊት ሲጠቀሙባቸውና ለኢትዮጵያ የሚታገለውን ወገን እንዲህ በአደባባይ እየጠለፉ ሲጧዙ፣ አፍራሽ ድርጊታቸውን ማውገዝ የሁላችንም ግዴታ ነው።

ቅንጅት አንድ ነው!
ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ትግል ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች!

የቅንጅት ደጋፊዎች
ከኦክላንድ

ጀንዋሪ 23 ቀን 2008